# ቴዲ አፍሮ በለንደን ፍቅርን ሰበከ



በአባተ መላኩ
abatemelaku@gmail.com

ከኢኮኖሚው ውድቀት ጋር ተያይዞ ይሁን አይሁን ባይታወቅም ወቅቱ ዘፋኝን አስመጥቶ ማትረፍ አይደለም ዋናን ማስመለስ እንደ ስኬት የሚቆጠርበት ጊዜ ነው::

የፈረንጆች ገና ማግስት በለንደን ቴዲ አፍሮን ከአድናቂዎቹ እንዲሁም እንዲፈታ የታገሉለትን ወንድም እህቶቹን ያገናኘቻችው ቀን ነበረች ፤ ዝግጁቱ የተዘጋጀው ከ2000 ሰው በላይ በሚይዘው ደቡብ ለንደን ከሚገኝ ትልቅ አዳራሽ ውስጥ ነበር ::

ቴዲ የሚመጣበትን ቀን ካበሰረው በራሪ ወረቀት ጋር «ቴዲ እውቅ ያደረገውን ዘፈኑን መዝፈኑን አቆመ ፤ ከዘፈነውም እንዳልነበረ ቆራርጦ ነው የሚዘፍነው» የሚሉ ዜናዎች ቀድሞ ከተጫወተባቸው አንዳንድ የአውሮፓ ሀገራት ሲናፈሱ ፤ በለንደን የሚገኙ የክፉ ጊዜ ወዳጆቹን እጅግ አስደነገጠ::

ከዛም በመቀጠል ትናንት ስለደረሰበት ግፍ የአየር ሰዓታቸውን ሰተው ያስተላለፉ ፤ ብእራቸውን አንስተው የጻፉ የሚዲያው ተቋማት «ቴዲን ማነጋገር አልቻልንም» «ልናገኘው በጭራሽ አልተቻለም» በማለት ያስተላለፉት ዜና ተጨምሮበት አንዳንድ የለንደን ወዳጆቹን በዝግጅቱ ላይ መገኘታቸውን ሁለት ጊዜ እንዲያስቡበት አድርጓቸው ነበር ፤ ሆኖም ወሬውን ትተን የሚለውን እንስማ ብለው ወሬ ሳይበግራቸው በቦታው ላይ ብዙዎቹ ተገኙ::

በእስር በነበረ ጊዜ ሲወቅሱት እና «የተፈረደበት ፍርድ አነሰው» ሲሉ የነበሩት ሁሉ አሁን አድናቂዎቹ ሆነው አዳራሽ ውስጥ ለመግባት ተሰልፈዋል::

በሌላ ወገን ደግሞ ቴዲ ምንም ይሁን ምን እንወደዋለን እናደንቀዋለን ስለዚህ ገብተን አብረን ፍቀርን እናዜማለን የሚሉም ነበሩ::

ሙዚቃው የተዘጋጀበት አዳራሽ ውስጥ መግባት መቻል ራሱን የቻለ ድል ነበር ፤ ሁሉም በየፊናው ለመግባት የሚያደርገው ትንቅንቅ የሚያስገርም ሌላ ትርኢት::

ዝግጅቱ ከሚጀመርበት ከ 4 ሰዓት በፊት ጀምሮ አዳራሹ ውስጥ ለመግባት ሰልፍ የተሰለፈው ታዳሚ አንዳንዱ ስርዓት ጠብቆ ተሰልፏል ፣ ሌላው መሰለፍ እንደማያዋጣ ተገንዝቦ መግቢያው በር ጋር ተደርድሮ አጋጣሚን ይጠባበቃል ፣ ሌላው ሚያውቀውን ሰው ፈልጎ ጣልቃ ይገባል ፣ ሌላው በዚህ ተበሳጭቶ ይጋጫል ፣ አንዳንዶች ከ300 ሜትር በላይ የረዘመው ሰልፍና የዝግጅቱ የመጀመርያ ሰዓት መዳረስ የመግባታቸውን ተስፋ አስቀርጧቸው ጥለው መሄድ ጀምረዋል ፤ ይህንን ሳስተውል ሀገራችንና ፖለቲካችን ትዝ አለኝ::

እድሉን አግኝተው አዳራሹ ውስጥ ለተገኙት ከ2000 በላይ ለሚሆኑት ታደሚዎቹ ቴዲ አፍሮ እና አቡጊዳ ባንድ እኩለ ለሊት ላይ የሙዚቃ ድግሳቸውን ማቋደስ ጀመሩ





መድረክ ላይ እንደወጣ በእስር በነበረ ጊዜ በተለያየ መልኩ ያሰቡትን ፣ ተሰልፈው የጮሁለትን ወገኖቹን በትህትና ተንበርክኮ ምስጋናውን ገለጸ:: ማድረግ አለብኝ ብሎ ሳይሆን ከልቡ ለህዝብ በአክበሮትና በምስጋና ሰገደ:: ህዝቡም በሰሜት አጨበጨበ ፣ ጮኸ ፣ አፏጨ::
ቴዲም «ትወዱኛላችሁ?» ብሎ ጠየቀ ፤ «አዎ» አለ ህዝቡ በጩኸት ፤ ደግሞ «ትወዱኛላችሁ?» ብሎ ጠየቀ ፤ ከበፊቱ በጨመረ ድምጽ «አዎ» አለ ህዝቡ ፤ የሚቀጥለው ጥያቄው ግን እንዲሁ በቀላሉ የሚመለስ አልነበረም ፤ «እናንተስ ትዋደዳላችሁ?» አለ ፤ ህዝቡም « . . . .አዎ» ብሎ መለሰ ቴዲም ማሉ ብሎ ክርስቲያኑን በእግዚአብሄር እስላሙን በአላህ አስማለ::
የእውነት ግን እንዋደዳለን?

«ቴዲ ንጹህ ነው! ፍቱልን!» በማለት ኤምባሲ ፊት ለንቃቸው እስኪበጠስ ሲጮሁ የነበሩትና በቅርቡ በተናፈሰበት ወሬ የተደናገጡት ዛሬ ግን በደስታ ሰክረውና ሲቃ ተናንቋቸው
«በ17 መርፌ በጠቀመው ቁምጣ
ለለውጥ ያጎፈረው ዙፋን ላይ ሲወጣ
እንዳምናው ባለቀን ያምናውን ከቀጣ
አዲስ ንጉስ እንጂ ለውጥ መቼ መጣ
ይቅር በለውና የበደለን ወቅሰህ
ምህረት አስተምረን እንደ አርገን መልሰህ» በማለት አብረውት አዜሙ::



የኤርትራም ልጆች ፣ ሶማሌዎች ፣ ጀማይካኖች ፣ ነጮችም እንዲሁ በአዳረሹ አብረው ፍቅርን አዜሙ

ሙዚቃው የተዘጋጀበት አዳራሽ የሚገኝበት ሰፈር ኤለፋንት ኤንድ ካስትል ሲባል ቀጥተኛ የአማርኛ ትርጉሙ ዝሆንና ቤተ መንግስት ነው አጋጣሚም እንበለው የእግዚአብሄር ረቂቅ ጥበብ
«ዝሆኖች ተጣልተው ሰበሩት ድንበሩን. . . . .»
«በዝሆን ጠብ ሲጎዳ ሳሩ
ዝም አይልም ያያል እግዜሩ» የሚል ስንኝ ያለውና የኢትዮጵያንና የኤርትራን ህዝብ አንድነት ወን ድማማችነት የሚያስረዳው ዘፈኑ ተሰበከበት::

በአዳራሹ ውስጥ የተገኙት ከኢትዮጵያውያን ያላነሱ ኤርትራውያኖች ከቴዲ ጋር አብረውት ዘመሩ::

ቴዲ በዘፈኑ ፍቅርን ሰብኳል ፤ በፍቅሩ የተለያዩን ህዝቦችን አገናኝቶ ፍቅርን እንዲያዜሙ አድርጓል ፤ በደም የተለያዩን ወገኖችን በጥበብ አገናኝቶ የፍቅር ማእድን ጋብዟል::
«ማንንም አትጥሉ . . ተዋደዱ . . ይያያዝ እጃችሁ» ብሏል «የተያያዘ እጅ ጠንካራ ነው ፤ ፍቅር ካለን አንራብም ፍቅር ካለን እናድጋለን ብሎ መክሯል»

«እነሱ ስላልተስማሙ ተለያዩ እኛ ደግሞ ስለምንስማማ በፍቅር አንድ እንሆናለን» ብሏል
የሙዚቃው ንጉስ ጥላሁን ገሠሠ በትረ ስልጣኑን ለቴዲ አፍሮ አስረክቦ  አልፏል ቴዲ አፍሮ ንግስናውን አላቃለለም ፣ እኛንም አላሳፈረም ፤ አገሩን ወዶ በልጅነት እድሜው የመከራን አለንጋ ቀምሶ ለሀገር ባለው ፍቅር ልባችን ውስጥ ነግሷ ል::

ለሀገር ያለው ፍቅር ፣ ለህዝበ ያለው ትህትና ፣ ለሙያው ያለው ክብር ፣ ከእግዚአብሄር በተሰጠው ጸጋ ሳይዘፍን ያስታውቅበታል ፤ አንደበቱን ሳይከፍት ተናግሯል ፤ መረዳት የኛ ፈንታ ነው!

ቴዲ አፍሮ ጸጋውን አሸቀንጥሮ የሚጥል ሞኝም ሰው አይመስልም:: «50 ሺ ሰው እንዲያጨበጭብልኝ ያረገ እግዚአብሄር 50 ሺ ሰው ድንጋይ እንዲወረውርብኝ ማረግ እንደሚችል እንዳልረሳ እንዲያረገኝ እለምነዋለሁ» ሲል ተሰምቷል:: ሁላችንም በየህይወታችን ያንን ባንረሳ አሁን ካለንበት መከራ በቀላሉ በወጣን ነበር::

ቴዲ አፍሮ ፍቅርን እየዘመረ ፣ ለታላቅ ታናሾቹ ተዋደዱ ይቅር ተባባሉ እያለ ፣ እሱ ላይ ክፉ ማድረጋችን ፣ ክፉ ማውራታችን ወይም ክፉ ማሰባችን ራሳችንን እንድንፈትሽ ያስገድደናል ፤ ለኢትዮጵያ ትንሳኤ የምንጨነቅ ሁሉ በልብም በመንፈስም ቴዲ አፍሮን እንረዳው እናድምጠው ሙዚቃው የመንፈስ ቋንቋ ነውና::

የታደላችሁ ሁሉ በየዝግጅቶቹ ላይ ተገኝታችሁ የፍቅሩን ማእድ ተቃመሱ ፣ የትንሳኤውን ጥሪ አድምጡ ፣ በተስፋ ትጸናላችሁ በሀሴት ትረካላችሁ::

